# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል

## 29 ኛ ሳምንት

## የኤማሁስ መንገደኞች

**ዓላማ**

- ስለ ክርስቶስ ትንሣኤና እንዴት ለኤማሁስ መንገደኞች እንደተገለጠ መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**

- "ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ? ተነስቶአል እንጂ በዚህ የለም።" ሉቃ 24፣5-6

**ምንባብ**

- ሉቃ. 24፣13-15

**መግቢያ**

- ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኂላ በሦስተኛው ቀን ተነሣ መጀመሪያ ከቅዱስን አንስት።ከዚያ ለሌሎች ደቀመዛሙርቱ ተገለጠ።
- በዛሬው ትምህርታችንም ከእነዚህ መገለጦች የኤማሁስ መንገድ የሆነውን እንማራለን።

**ትምህርቱ**

- በጌታ መቃብር የተገለጠላቸው መልአክና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለመግደላዊት ማርያም ሁለት ደቀመዛሙርት ከኢየሩሳሌም ወደ ኤማሁስ ሄዱ።
- በመንገዳቸውም ክርስቶስ ሊሠቀል ስለነበረው ሁኔታና ስለተፈጸሙት ተዓምራት ይነጋገሩ ነበር።በዚህ መሐል ጌታችን ከጎናቸው ሆኖ ስለሚነጋገሩት ይጠይቃቸው ነበር።
- እነርሱ ግን አላወቁትም ስለምን እያወራችሁ ነው ሲላቸውም ***"በኢየሩሳሌም ብቻህን ትኖራለህ? ወይስ በነዚህ ቀናት የሆነውንስ እንዴት አታውቅም?"*** ጌታችን ኢየሱስም መልሶ ***"ምንድን ነው?"*** አላቸው።
- ኢየሱስ የተባለ ነቢይ እንደተነሣና ብዙ ድንቆችን እንደፈጸመ፣የካህናት አለቆችና መኳንቶቻቸው ግን ለሞት አሳልፈው እንደሠጡት፣እስራኤልን ይዋጃል ብለው ይጠብቁት የነበረው ግን እርሱን እንደነበር ነገሩት ከሞተ ሦስት ቀን እንደሆነውና፣
- ሴቶች ግን በመቃብሩ ሥፍራ ሥጋው እንደሌሉና መነሣቱንም እንዳረጋገጡ ነገሩን አሉት።
- ጌታችንም ልባቸው ከማመን የዘጋየ መሆኑን ወቅሶ ክርስቶስ ይሄን ሁሉ መከራ ይቀበል ዘንድ አስቀድሞ ለነቢያት እንደተናገረ አስረዳቸው። በክብር እንደሚነሳም አበሰራቸው።
- ወደ መንደሩ ሲደርሱም ስለመሸ ከነርሱ ጋር እንዲቆይ የግድ ብለው ለመኑት።ወደ ቤት ከገቡና በማዕድ ከተቀመጡ በኂላ ባርኮ የሚበሉትን ሰጣቸው ዓይኖቻቸው ተከፈቱ እርሱ መሆኑንም አወቁ።ከዚያም ተሰወራቸው።
- ሲያስተምራቸው ልባቸው ይቃጠልባቸው እንደነበርና መጻሕፍትም እንደገለጠላቸው አስተዋሉ።ወደ እየሩሳሌምም ተመልሰው በኤማሁስ መንገድ የሆነውን ነገሩት

**ጥያቄዎች**

1. ጌታችን ከተነሳ በኂላ በመጀመሪያ የተገለጠው ለማን ነው?
2. በኤማሁስ መንገዶች ስለምን ነበር የሚያወሩት? ጌታችን ለኤማሁስ መንገደኞች ምን ነገራቸው?
3. የኤማሁስ መንገደኞች የሚያናግራቸው ክርስቶስ መሆኑን መቼ አወቁ?

**መዝሙር**

ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ
ተኃጺባ በደመ ክርስቶስ

ምድርም በክርስቶስ ደም ታጥባ
ፋሲካን (ደስታ) ታደርጋለች።

**ይቆየን።**